# የኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር (ካላንደር) ታሪክ ባጭሩ

ከታደሰ ገብረኪዳን

## መንደርደሪያ

በኢትዮጵያውያንም ሆነ በአውሮጳውያን ቀን አቆጣጠር መሰረት የአመት እርዝማኔው 365 ቀን ከሩብ ነው። ሁለቱም አቆጣጠሮች መነሻ ያደረጉት ክርስቶስ የተወለደበትን አመት ነው። ታዲያ ሁለቱ አቆጣጠሮች ለምን በሰባት አመት ተለያዩ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ከፊታችሁ ቆሜአያለሁ።

አሻሮ ዘግኖ ወደ ቆሎ ጠጋ እንዲሉ አጋጣሚውን በመጠቀም ስለኢትዮጵያዊነትና ስለጥንት ኢትዮጵያውያን ከሳይንስ መዝገብ ያገኘሁትንና ከታሪክ ማህደሮች ፈልፍዬ ያወጣኋቸውን ዕጹብ ድንቅ ታሪኮች ከቀን ቆጠራ ታሪክ ጋር አሰባጥሬ ላቀርብ ተዘጋጅቻለሁና ጆሮዎቻችሁን እንድታውሱኝ እለምናለሁ። ታሪኮቹ የተወሱት ለዘመን ቆጠራ አመጣጥ በተዘዋዋሪም ቢሆን አስተዋጽዖ ስላላቸው ነው።

ከመነሻው ሁለት ነጥቦችን ማስገንዘብ እፈልጋለሁ። አንደኛ፣ የቀን አቆጣጠር ታሪክ ከመመርመራችን በፊት ስለሰው ልጅ ፍልሰት ታሪክ መዳሰስ ተገቢ ይሆናል። ይህን የምናደርገው በዛሬው ዕለት እዚህ የተሰበሰብነው የዘመኑ ፈላሾች ስለሆንን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያውያን በመሆናችንም ጭምር ነው። ምን ለማለት እንደፈለግሁ ከገለጻዬ ትረዳላችሁ ብዬ አምናለሁ። ሁለተኛ፣ የኢትዮጵያውያን ቀን አቆጣጠር ስርአትን ለመረዳት ስለ ጥንት ግብጻውያንና ሮማውያን አቆጣጠር ማወቅ ስለሚያስፈልግ ስለሁለቱም አጭር መግለጫ ይቀርባል።

## የሁላችንም እናት

ዛሬ በዚህ ስፍራ የተገናኘነው 2000ን ለመቀበል ነው። እንኳን ለዚህ ያደረሰን ካልኩ በኋላ ይህን የተቀደሰ ቀን የዛሬ 160000 አመት ሊፈጸም ተቃርቦ የነበረው ክስተት ሳይፈጸም በመቅረቱና የሰው ልጅ ህልውና ተረጋግጦ እዚህ ለመድረስ በመቻላችን ምስጋና ለማቅረብና ስለወደፊቱ ዕድላችንም ለማሰብ ጭምር ብናውለው ተገቢ ይመስለኛል።

የሰው ልጅ ሁሉ እናት በምድራችን በአፋር ከ3 ሚሊዮን አመት በፊት የኖረችው ኩሩሩዋ ድንቅነሽ ስለመሆንዋ ያልሰማ ቢኖር የዘለአለም እንቅልፍ የተኛ ብቻ ነው። ቀጥሎ የምናገረውን ያለሰማ ካለ ግን ብዙም አልደነቅም፣ ምክንያቱም የዲኤንኤ (DNA) ምርምርን መሰረት ያደረገው

የሰው ልጅ ፍልሰት ታሪክ ህዝብ እንዲያውቀው መደረግ የተጀመረው ገና ትናንት በመሆኑ ነው።

ማንኛውም ነፍስ ያለው ፍጡር፣ ዕጽም ሆነ እንስሳ፣ ህይወት ኖሮት መመገብ፣ ማደግና የርቢ ተግባር መፈጸም የሚችለው ከዚያም ወደ ግዑዝነት የሚለወጠው በውስጡ ተቀብሮ ወይም ተጽፎ በሚገኝ ከስኳርና ፎስፌት አተምስ (sugar and phosphate atoms) የተሠራ ዲኤንኤ (DNA) የተሰኘ ዕጹብ ድንቅ ማስተርፕላን ወይም ብሉፕሪንት አማካይነት ነው። ይህ ለህይወት መሰረት የሆነው ረቂቅ ነገር ወይም ማተር ነው እያንዳንዱ ፍጡር እንዴት እንደሚገነባና እንደሚሠራ ትዕዛዝ የሚሰጠው። ዲኤንኤ ስለመኖሩ ከታወቀ ገና 50 አመት ያህል ብቻ ነው። ማስተር ፕላኑን የፈጠረው ማነው? ለሚለው ሃይማኖተኞች እግዚአብሄር ነው ሲሉ አብዛኛ ዎች ሳይንቲስቶች ግን ኢቮሉሽን ነው ይላሉ። ለጊዜው እንዲያው ዝም ይሻላል፣ በተለይ እዚህ የተገኙት የነፍስ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት መቋሚያ ይዘው ከሆነ!

የድንቅነሽ ዝርያዎች ከምድረገጽ ላለመጥፋት ካራዊት፣ ከበሽታ፣ ከእሳተገሞራ፣ ከመሬት መንቀጥቀጥና ከጎርፍ ጋር ሲታገሉና እግረመንገዳቸውንም ህልውና የማረጋገጥ (survival) ስልታቸውን እያዳበሩ ቢቆዩም ኑሮን መቋቋም በጣም ከብዷቸው ኖሮ ካለፈው ትውልድ በአደራ የተረከቡትንና ሰውን ሰው ያሰኘውን ዲኤንኤ ተከባክቦ ማቆየትና ለወደፊቱ ትውልድ ማስተላለፍ ወደማይችሉበት ደረጃ ደርሰው ነበር።

የሰው ልጅ ህልውናው የተረጋገጠው የዛሬ 160000 ዓመት ገደማ በኛ ው የኦሞ ሸለቆ የኖረችው ቅመአያታችን በህይወት ቆይታልንና ዘር አፍርታ በማለፏ ነው። ከሷ በፊት የኖሩት ሴቶች የወለዷቸው ሴቶች ልጆች ዝርያቸው በምድር ላይ አይገኝም። አሁን በመላው ዓለም የምንገኘው ከ6 ቢሊዮን በላይ ሴቶችና ወንዶች ሁላችንም የኦሞዋ ቅመአያታችን ልጆች ነን። እሷ ተርፋ ሴቶች ልጆች አፍርታ ባታልፍ ኖሮ ዛሬ በዓለም ላይ የሰው ዘር የሚባል ፍጡር አይኖርም ነበር።

በዓለም ላይ በምትገኙ ሴቶች በሙሉ በውስጣችሁ የኦሞይቱ እናታችንና ከዚያም በኋላ የነበሩት እናቶቻችን አሻራ ተጽፎ ይገኛል። በዚህ አጋጣሚ፣ በኦሞ ሸለቆ ትልቅ የሴት ሃውልት እንዲሠራና ያለም ህዝቦች እየመጡ እንዲሰግዱላት ሃሳብ አቀርባለሁ። ሴቶችም ከኦሞዋ እናታችን ባደራ የተቀበላችሁትን የታሪክ ማህደር ከወንዶች ጋር እየተባበራችሁ የማስተላለፍ ግዴታ እንዳለባችሁ ሳላስገነዝብ ማለፍ አልወድም።

የሰውን ዘር ሊያጠፋ የሚችል ሰው ሠራሽ ወይም ተፈጥሮአዊ ክስተት ነገ አፍጥጦ ሲመጣ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት የሰው ዘር ዲኤንኤን አላስነካ ባይዋ የልጅ ልጃችን ከየት ይሆን ብቅ የምትለው? ከቲምበክቱ ወይስ ከኪሪባቲ? ከቶንጋ ወይስ ከካምቻትካ? ከኦታዋ ወይስ ከየሳንቃ? ከኔፓል ወይስ ከሞልዶቪያ? ማን ያውቃል?

የሰው ዘር ያለፈበትን ወይም ያለፈውን ቆም ብሎ ሲያስብ ባንጻሩ የወደፊት ህልውናውን እንዴት እንደሚያስጠብቅ የጋራ ተግባሩ ሊያደርገው ይገባል:: ሆኖም፣ የሰው ልጅ ዕውቀቱንና ያካበተውን ብልሃት ለህይወት ክብካቤ ሳይሆን ወንድሙን ለመግደል ወይም ተፈጥሮን ለመፈታተን እስካዋለው ድረስ ፈጣሪው የሆነው ተፈጥሮ ተቆጥቶ አስቸጋሪውን ፍጡር መልሶ እከርሱ ውስጥ ማስገባቱ አይቀሬ ነው:: የሰው ልጅ ካልጠግብ ባይነቱና ዓለም የተፈጠረችው ለሱ ለብቻው መፈንጫ፣ መራገጫና ማጌጫ ብቻ ነው ከሚል ከተሳሳተ እምነትና ከራስ ወዳድነት የተነሳ ያወደማቸው ዕጽዋትና አራዊት የምስክርነት ቃል የሚሰጡበት ወቅት ሲደርስ ጉድ መፍላቱ አይቀርም:: የሰው ልጅ ጠባዩንና አካሄዱን አስተካክሎ ካራዊትና ከእጽዋት ጋር ተስማምቶ ቢኖርም በተፈጥሮ ህግ መሰረት ጥፋትና ፍጥረት (destruction and creation) ስለማይነጣጠሉ የሰው ልጅ ሌላ **160000** ዘመን እንደሚያከብር ምንም ማረጋገጫ የለም:: ቢሆንም፣ ተስፋቢስ ከመሆን ተስፈኛ መሆን ስለሚመረጥ የሰው ዘር ዕድሜ ገደብ አልተበጀለትም ብሎ መንዝ ይሻላል::

## <u>የሰው ልጅ ፍልሰት</u>

የሰው ልጅ የፍልሰቱ አቅጣጫና የፈለሰበት አማካይ ዘመን የተረጋገጠው በየክፍለ ዓለማቱ በሚገኙ ሰዎች በተለይም በተለምዶ አነጋገር ኋላ ቀር በምንላቸው ጥንታዊ ማህበረሰቦች ላይ በተደረገ የዲኤንኤ ምርምር ነው::

ሁሉም ፍጡር ዲኤንኤውን ከወላጆቹ የወረሰው በመሆኑ ዲኤንኤ የሰው አመጣጥ ታሪክ ማህደር ነው:: ሆኖም፣ ሊታወቅ የሚገባው፣ መዝገቡ የሚገኘው ሴትነትን በሚወስነው በሴቶች ውሰጥ በሚገኘው ኤክስ ክሮሞዞምስ (X Chromosomes) ውስጥ ብቻ ነው:: ሴቶች የልጅና የቤት ጣጣ ብቻ ሳይሆን የሰው ዘር አመጣጥ መዝገብም ተሸካሚዎች በመሆናችሁ ወንዶች በአንድ ላይ ሆነን ውለታሽ በዛብኝ የሚለውን መዝሙር ደጋግመን ልናዜምላችሁ ይገባል::

አሁን ወደፍልሰቱ ታሪክ በቀጥታ እናምራ:: የፍልሰቱ አቅጣጫና ዘመኑ በግምት ከዚህ በታች ተመልክቷል::

<u>ዘመን</u>

***160000*** በኦሞ ሸለቆ የኖረችው ቅመአያታችን ሴት ልጅ ወልዳ አለፈች::

***140000*** የልጅ ልጆቿ ከኦሞ ሸለቆ ተነስተው ወደአፋር፣ ምዕራባዊና ደቡባዊ አፍሪቃ ፈለሱ::

| | |
|---|---|
| ***130000*** | በግብጽ ምዕራባዊ ዳርቻ አድርገው ኢራቅ ደረሱ:: |
| ***100000*** | ኢራቅ የደረሱት አለቁ:: |
| ***80000*** | ከአፋር መሬት ተነስተው በአረብያ አድርገው ህንድ፣ ኢንዶኒሺያ፣ ኢንዶቻይና ዘለቁ:: |
| ***74000*** | ሱማትራ ከሚገኘው ቶባ ከሚባለው ተራራ እሳተገሞራ ፈንድቶ ህንድ ውስጥ የሰፈሩትን ከሞላ ጎደል ሁሉንም አጠፋቸው:: |
| ***70000*** | አውስትራሊያና አካባቢው ደሴቶች ደረሱ:: |
| ***55000*** | ከአሁኑ ባንግላዴሽ አካባቢ ተነስተው ቱርክ ደረሱ:: |
| ***50000*** | ወደ አውሮጳ ተሻገሩ:: |
| ***45000*** | መካከለኛው እስያ ዘለቁ፣ በግብጽ በኩል አድርገው ሰሜን አፍሪቃ ገቡ:: |
| ***37000*** | ሩቅ ምስራቅ፣ መካከለኛው አውሮጳ፣ ሰሜን አውሮጳ ደረሱ:: |
| ***25000*** | ከሩቅ ምስራቅ ተነስተው በአላስካ በኩል አድርገው ሰሜን አሜሪካ ገቡ:: |
| ***20000*** | ሰሜን አውሮጳ፣ ሰሜን እስያ፣ ሰሜናዊው ሰሜን አሜሪካ፣ አንታርዮ ጭምር፣ በበረዶ ስለተሸፈኑ በነዚህ ቦታዎች ሰፍረው የነበሩት አብዛኛዎቹ ሲያልቁ የተረፉት ወደ ሞቃታማ ስፍራዎች አፈገፈጉ:: |
| ***17000*** | ከሰሜን አሜሪካ ተነስተው ደቡብ አሜሪካ ዘለቁ:: |
| ***14000*** | ከሰሜን አሜሪካ ወደ ደቡብ አሜሪካ በብዛት ጎረፉ:: |
| ***9000*** | በሰሜኑ ክፍለ ዓለማት ተኝቶ የነበረው በረዶ ስለቀለጠ አካባቢዎቹን ሰዎች መልሰው ሰፈሩባቸው:: እርሻም ተጀመረ:: የሰው ዘር ለማህበራዊ ኑሮ መሰረት ጣለ:: |

ይኸው፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ዓለምን ከዳር እስከ ዳር ወርረን ሰፍረንባታል ማለት ነው!

የሰው ዘር የተፈጠረበትን ኢትዮጵያን የተረከብነው ሰዎች ለብዙ ሺህ አመታት ብንፋግርም ኑሮ ሳይሳካልን ቀርቷል:: ብዙዎቻችንም ለስደት ተዳርገናል:: ሆኖም፣ ዝርያዎቻችን በተለይም ባውሮጳና በሰሜን አሜሪካ የሚገኙት ስላለፈላቸው እነሱስ እነማን ሆኑና? ያው የኛው ልጆቻ አይደሉም? የደላንም እኛ የተጎሳቀልንም እኛው ማለት ይቻል ይሆናል:: ይህም ሲባል የተሳካለት የሩቅ ዘመዳችንን ስናይ አጎቴ ነው የምንል፣ ባንጻሩ ከተጎሳቆሉ ግን እናትና አባታችንን ሳይቀር እስከመካድ የምንደርስ ፍጡሮች መሆናችንን ሳይረሳ ነው::

ድሮ ኤትዮጵያዊ ነኝ ለማለት እሽቅድምድም ያልያዝን ያህል በተለይ ከ1964/65 ድርቅ በኋላ ዜግነቱን ለመሸሽግና ኢትዮጵያዊነት ለምኔ ያለው ጥቂት እንዳልሆነ ይታወቃል:: የክስተቱ መዘዝ አሁንም እተፈታተነን ነው ያለው:: የመገንጠል ስሜት የተፋፋመው ከዚያ

በኋላ ነው:: ሆኖም፣ የኢትጵጵያ አምላክ የሚፈታተኑትን የማይወድ ነው:: አሳር ሳያሳያቸው የሚያርፍ አይነት አይደለም:: በዚህ ረገድ ብዙ አይተናል፣ አሁንም እያየን ነው፣ ወደፊትም ይታያል:: እናታችን ኢትዮጵያ ለዘለአለም ትኑርልን::

ሌላው ባስመዘገበው ውጤት ስለመኩራራት ሲነሳ የዛሬ 34 አመት እንግሊዝ አገር በስልጠና ላይ በነበርኩበት ወቅት ያደመጥኩትን ቃለመጠይቅ ያስታውሰኛል:: ተጠያቂው የአገሪቱ አንድ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ናቸው:: እንግሊዝ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ድቀሳ በሚገባ ማንሰራራት ባለመቻልዋ ችግሩ ካመራር ጉድለት ወይስ ከሌላ ስለመሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይጠየቃሉ:: ሲመልሱ እንዲህ አሉ:- «አቶ ጠያቂ፣ ስማኝ፣ ጉዳዩን በውል አልተረዳኸውም፤ የእንግሊዝ ህዝብ እኮ ከማንም ይበልጥ ልቆ ሄዷል፣ ይህን ለመመስከር አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ኒውዚላንድ፣ ድቡብ አፍሪቃ፣ ድቡብ ሮዲሺያን ሄዶ ማየት ነው» አሉት:: በጊዜው፣ አባባሉን፣ የተቀደመ ህዝብ እራሱን የሚያታልልበት ፈሊጥ ብዬ ነበር ያለፍኩት:: ጉዳዩን አሁን ጠጋ ብዬ ስመረምረው የሰውዬው አባባል እውነትነት አለው:: ለቅኝ አገዛዝና ለቡጥቦጣ እንዲያመቻቸው ያለም ህዝቦችን በልዩ ልዩ ዘዴ ከፋፍለውና አናቁረው በየቦታው ካንሰር የዘሩ እንግሊዞች አሜሪካንን የበላይ ጠባቂና ተገን በማድረግ ካናዳን፣ አውስትራሊያን፣ ኒውዚላንድንና ጥገኞቻቸውን በማስተባበር የእንግሊዝኛ ተናጋሪ አገሮች በበላይነት እንዲቀዩ ያላሰለሰ ሙከራ ሲያደርጉ ሳይ ዋዛዎች አይደሉም እላለሁ::

የመከፋፈሉን ሳይሆን አንድ የማድረጉን ስልት እኛ ኢትዮጵያውያንም ብንካንበት የሰው ዘር ምንጭ የሆነውን አገር ህዝብ ህልውናውን እናቀይለት ነበር:: ይህንን ማድረግ ከተሳነን ግን የ2000 አከባበር የኋላ ኋላ የቁም ተዝካር ስብሰባ ተብሎ በታሪክ አዋቂዎችና ተራቢዎች መፈረጁ አይቀርም:: ከዚህ ያድነን::

## ቀን አቆጣጠር በተለያዩ አገሮች

አሁን ወደ ተነሳንበት ወደ ቀን ዘመን ቆጠራ ታሪክ እናምራ:: በጥንት ስልጣኔያቸው የታወቁት፣ ለምሳሌ፣ ግሪኮች፣ ሮማውያን፣ ባቢሎናውያን፣ እብራውያን፣ የቻይና ሰዎች አቆጣጠራቸው የተመሰረተው ጨረቃ በመሬት ዙሪያ ከምታደርገው መሽከርከር ወይም በተራ አነጋገር ከጨረቃ መታየት ጋር ነበር:: ስለሆነም፣ የወራት ሂደት ወይም መፈራረቅ ከቀን አቆጣጠር ጋር አልገናኝ እያሉ ይፈጠር የነበረውን ችግር ለመቋቋም ተጨማሪ ቀኖች አልፎ አልፎ ባስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲገቡ ይደረግ ነበር::

የዘመን አቆጣጠር በየአገሩ የራሱ ታሪክ ያለው ነው:: ጃፓኖች ካላንደር ሠርተው ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙት ገና የዛሬ 1400 አመት ገደማ ነው:: ዘንድሮ እንደኛ አቆጣጠር 2000፣ እንደ አውሮጳውያን 2007፣ እንደ ኢራንያኖችና አፍጋኒዎች 1386፣ እንደሌሎቹ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች 1428፣ እንደ ቻይኒዞች 4704፣ እንደ አርመኖች 1455፣ እንደ አይሁዶች ድገሞ 5767 ነው:: ቁጥሩን የሚወስኑት ቆጠራው የተጀመረበት አመትና አቆጣጠሩ የተመሰረተው በጨረቃ ወይም በጸሃይ አሽክርክሪት ላይ መሆን አለመሆን ናቸው::

አመቱ ሺ በደፈነ ቁጥር የዓለም ፍጻሜ የተቃረበ እየመሰለው የሚሸበረው ሁሉ የዘመን ቁጥሩ ወዳልደፈነ አገር ማምለጥ ስለሚችል ለድሃ ይብላኝለት እንጂ ሃብታሙማ ማድረግ ያለበት የመጓጓዣ ቲኬት መግዛት ብቻ ነው::

## የጥንት ግብጽ ዘመን አቆጣጠር

የእርሻ ጥበብ ካዳበሩትና ለሥልጣኔ ዋና ምንጭ ከነበሩት ህዝቦች መካከል ግብጻውያን በግንባር ቀደም የሚጠቀሱ ናቸው:: እንግሊዞች necessity is the mother of invention እንዳሉት የጥንት ግብጻውያን በእርሻ ሥራ የተራቀቁት ለዝናብ ስላልታደሉና ሳይተርፋት አበደረች እንዲሉ እናታቸው ኢትዮጵያ የምትልክላቸውን ውሃና አፈር በቅጡ ከመጠቀም ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው ስለተገነዘቡ ነበር:: (በነገራችን ላይ የግብጽ መሪ የነበረው አንዋር ሳዳት ባንድ ወቅት ስለሁለቱ አገሮች ግንኙነት ሲናገር ኢትዮጵያ እፍታዋን (ማለትም አፈርዋንና ውሃዋን) እስከገበረችን ድረስ ከሰዎቿ ጋር ምንም ጉዳይ የለንም ያለውን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በልቡ ውስጥ አኑሮ ከትውልድ ትውልድ ማስተላለፍ የሚገባው ጉዳይ ነው::)

የጥንት ግብጻውያን የቀን አቆጣጠራቸው ከእርሻ ሥራ ጋር የተቆራኘ ነበር:: ይኸውም፣ አቆጣጠሩ የወራት መፈራረቅን አንጸባራቂ ነበር:: በዘመናዊ አነጋገር፣ አቆጣጠሩ መሬት በጸሃይ ዙሪያ ከምታደርገው መሽከርከር ጋር የተቆራኘ ነበር::

በግብጽ አመቱ 12 ወሮች፣ እያንዳንዱ ወር ደግሞ 30 ቀኖች እንዲኖሩት ተድርጎ ለረዥም ጊዜ ሲሠራበት ከቆየ በኋላ በጋና ክረምት ባሳቻ ወቅት ከተፍ እያሉባቸው ስለተቸገሩ ስለከዋክብት እንቅስቃሴ ጥልቅ ምርምር ለማድረግ ተገደዱ ወይም ተነሳሱ:: ውጤቱም የዛሬ 6000 አመት ገደማ የአምስት ቀኖች መጨመር ነበር:: ተጨማሪዎቹ ቀኖች ለታላላቅ አማልክቶቻቸው መታሰቢያ እንዲሆኑ ተወስኖ ያባይ ውሃ ሞልቶ መምጣት በታላቅ ጉጉት

እየተጠበቀ አምስቱን ቀኖች ህዝቡ በፈንጠዝያና ጸሎት ያሳልፋቸው ነበር፡፡

የጥንት ግብጻውያን አባይ ሳያሰልስ የህይወት መሰረት የሆኑትን ውሃና ምዕራባዊውን የኢትዮጵያ ክፍል በማራቆት በየአመቱ 30 ቢሊዮን ኩንታል ያህል አፈር ተሸክሞ ከተፍ የሚልበትን ወር የወሮች ሁሉ በኩር ወይም መጀመሪያ አደረጉት፡፡ ስሙም ቱት ይባላል፡፡ የግብጾች አመት ብሎም ቱት የሚጀምረው በእኛ አቆጣጠር በመስከረም አንድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር ከየት እንደመጣ ከወዲሁ መገመት ይቻላል፡፡

የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ግብጽን የዛሬ 1400 አመት ገደማ ከወረሩ በኋላ ግን ከ5000 አመት በላይ የተሠራበት የቀን መቁጠሪያ ውድቅ ተደርጎ ወደ ጨረቃ ማንጋጠጥ ተጀመረ፡፡

## ጁሊያን ካላንደር

ጁሊየስ ሲዘር የሮማውያን ቀን አቆጣጠር መሰረቱን ከጨረቃ ወደ ጸሃይ እሽክርክሪት እንዲዞር አደረገው፡፡ ይህ የሆነው እአአ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ46 ነበር፡፡ ግብጾች ይከተሉት ወደነበረው ስርአት አዞረው ማለት ነው፡፡ ሌሎች ሁለት ተጨማሪ እርምጃዎችም ወሰደ፡-

አንደኛ፣ መሬት በጸሃይ ዙሪያ ለመሽከርከር የሚፈጅባት ጊዜ 365 ቀኖቸ ከስድስት ሰኣት መሆኑን ተገንዝቦ (ትክክለኛው ጊዜ 365 ቀን፣ ስድስት ሰአት፣ 11 ደቂቃ ከ15 ሴኮንድ ነው) የወራት መዛነፍን ለማስቀረት በየአራቱ አመት አንድ ቀን እንዲጨመር አዘዘ፡፡ አንድ አመት 365 ቀኖች ብቻ ሳይሆን 365 ከሩብ እንዳሉት ጁሊየስ ሲዘር የተረዳው ከግብጽ የከዋክብት ተመራማሪዎች ነው፡፡ የግብጽ ሰዎች ግኝቱን ወደ ተሻሻለ ቀን አቆጣጠር ሳይተረጉሙት በመቅረታቸው ጁሊየስ ሲዘር እርምጃ ወስዶ ስሙን አስተከለበት፡፡

ሁለተኛ፣ የግብጾችን አስራ ሶስተኛ ቁንጽል ወር አስቀርቶ 4 ወሮች እያንዳንዳቸው 30 ቀን፣ 7 ወሮች 31 ቀን እንዲኖራቸው አደረገና አስራሁለተኛው ወር ማለትም ፌብርዋሪ ለሶስት ተከታታይ አመታት 28 ቀኖች፣ ባራተኛው አመት ደግሞ 29 ቀኖች ይኑረው አለ፡፡

## የጀግናው ኢትዮጵያዊ የሜምኖን ሚና በትሮይ ጦርነት

ሮማውያን ታሪካችን የተጀመረው የሮማን ከተማ ሁለቱ ወንድማማቾች ሬመስና ሮምዩለስ ባቋቋሙበት በ753 አመተ ዓለም (ከክርስቶስ ልደት በፊት) ነው ይላሉ:: በዘመን አቆጣጠር ታሪክ አኳያ ሲታይ የተጠቀሰው አመት ከኢትዮጵያውያን ጋር የተገናኘ አስደናቂ ታሪክ ያለው ነው:: ታሪኩ እንደሚከተለው ነው::

ፓሪስ የሚባል የትሮይ ንጉስ ልጅ ወደ ግሪክ በእንግድነት ሂዶ ሳለ የስፓርታ ንጉስ የሜነላኦስን (Menelaus) ሚስት፣ ውቢቷ ሄለንን አስኮብልሎ ወደ ትሮይ ይዟት ይጠፋል:: ግሪኮች ሄለንን ለማስመለስ ያደረጉት ተደጋጋሚ ጥረት ባለመሳካቱ በትሮይ ላይ ጦርነት አውጀው በአሁኑ ጊዜ ቱርክ ውስጥ ወደምትገኘው ትሮይ በ1000 መርከቦች ተጭነው ዘመቱ::

ሄለን ምክንያት ትሁን እንጂ ወዳጄ ተስፋዬ ቀለታ እንደሚለው ጦርነቱ የሱሪ ነበር ለማለት ይቻላል:: ኤኮኖሚስቶች ደግሞ የጦርነቱ መሰረታዊ መንስኤ ባካባቢው የበላይነትን አረጋግጦ ንዋይ የመቦጥቦጥ ፍላጎት ነበር ይላሉ::

ጦርነቱ የፈጀው አስር አመት ሲሆን የፍጻሜውን 50 ቀናች ታሪክ፣ በኢልያድ (Iliad) የሰፈረውን፣ በግጥም ደርድሮ ያስተላለፈልን ኢትዮጵያውያን እንከን የማይገኝባቸው ሰዎች ናቸው ብሎ ያሞካሸን ታላቁ ገጣሚ አይነ ስውሩ ሆመር ነው:: ዳግመኛ ቢመጣ እንዴት ያዝንብን!

ጦርነቱ የተደመደመው በግሪኮቹ አሸናፊነት ነበር:: ከሞትና ባርነት የተረፉት ትሮጃንስ አንዳንዶቹ ወደ አውሮጳ ተሰድዱ:: ለብዙ መቶ አመታት ሲንከራተቱ ቆይተው ጣልያን የደረሱት የሮማን ከተማ ቆረቆሩ::

በዚህ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1194 እስከ 1184 በተደረገውና ለዘለአለም በሚታወሰው ጦርነት ኢትዮጵያውያን የተጫወቱት ሚና እጅግ አስደናቂ ስለሆነ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያውቀው ይገባል:: ታሪኩ የተፈጸመው ንግስተ ሳባ የሰለሞንን ጥበብ ለማድነቅ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጓዝዋ በፊት መሆኑ ነው::

ጦርነቱን ከፍጻሜ ማድረስ እንዲችል የትሮይ ንጉስ ፕሪያም ገናናው ጀግና ኢትዮጵያዊው ሜምኖን (Memnon) ጦር ይዞ እንዲደርስለት አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርግ በጊዜው በአሲሪያ (Assyria) ስር ለሚተዳደረው ለፐርሺያ አገረገዥ ለወንድሙ ለቲቶነስ (Tithonus) አስቸኳይ መልዕክት ያስተላልፍለታል:: ሜምኖንም

በአሁኑ ወቅት ምዕራብ ኢራን ዳርቻ ከምትገኘው ከሱሳ (Susa) ከተማ 1000 ኢትዮጵያውያንና 1000 ሲሲያንስ (Cissians) ምልምል ጦር ይዞ ከ200 የጦር ሰረገላዎች ወይም ቻርየትስ ጋር ወደ ትሮይ ተጓዘ:: በሱሳና በትሮይ መካከል የነበሩትን አገሮች ሁሉ እያስገበረና ያስቸገሩትን እየደመሰሰ አለፈ::

አሲሪያኖች ከደከሙ በኋላ የተነሱት ፐርሺያኖች እንዳሁኑ ዩናይትድ ስቴትስ የዓለም ገዥ ነን ለማለት በሚዳዳቸው ወቅት ሱሳ የኤምፓየራቸው ዋና ከተማ ነበረች:: ከተማዋ ስትቆረቆር ሜምኖን አንድ ፍሬ ልጅ ነበር::

ከተማዪቱን የመሰረተው የትሮዩ ንጉስ የፐሪያም ወንድም ቲቶነስ ቢሆንም የሜምኖን ከተማ ተብላ ትታወቅ ነበር:: የከተማዪቱ ነዋሪዎቸ ሲሲያንስ ይባሉ ነበር:: የሜምኖን እናቱ ስሟ ሲሲያ (Cissia) ስለነበር የከተማዪቱ ነዋሪዎች በሙሉ የሷ ልጆች እንደሆኑ ተወስዶ ሲሲያንስ ተባሉ:: የጥንት የአካባቢው ሰዎች ለኢትዮጵያዊው ሜምኖንና ለሌሎቹ ኢትዮጵያውያን የነበራቸው ግምት እጅግ ከፍተኛ ስለመሆኑ ከዚህ የበለጠ ማስረጃ አይገኝም::

በጀግናው ሜምኖን የሚመራው ጦር ግሪኮቹን ገጥሞ ባጭር ጊዜ ድል አደረጋቸው:: ዋና ዋና ተዋጊዎቻቸውን ሜምኖን በክንዱ አፈርድሜ አበላቸው:: ግሪኮቹ ወደመጡበት ለመመለስ ወደየመርከቦቻቸው ለመግባት ሲጣደፉ ምልምሉ ጦርም ተከታትሎ ፈጃቸው:: መርከቦቻቸውን ለማጋየት የነበረው ዕቅድ በተግባር ሳይተረጎም ቀኑ ጨለመ::

የግሪኮቹን ሃይል ለማጠናከር ከሰሜን ግሪክ ከቴሳሊ (Thessaly) የመጣ ጦር አድፍጦ ሜምኖንን ወግቶ ገደለው:: ምልምሉ ጦር መሪው መውደቁን ሲያይ ወደኋላው አፈገፈገ:: ግሪኮቹም እንደገና አንሰራሩና ለቀውት የነበረውን ስፍራ መልሰው መያዝ ቻሉ:: ኢትጵያውያኖቹ የጦርነቱን አውድማ ከለቀቁ በኋላ ግሪኮቹ አሸነፉ:: ትሮይንም አጠፏት::

እላይ እንደተገለጸው ከመገደል ያመለጡት ትሮጃንስ የልጅ ልጆቻቸው ሮምን ከ2760 አመት በፊት ቆረቆሩ:: ዘመኑንም የታሪካቸው መጀመሪያ ወይም መነሻ አደረጉት::

ጀግናው ሜምኖን ያተረፈው ዝና እጅግ የላቀ ስለነበር በጥንታዊቷ የግብጽ ከተማ በቴብስ (Thebes) ከጥቁር ድንጋይ የተሰራ በጣም ግዙፍ ሃውልት ቆመለት:: ሃውልቱን ያዩ ግሪኮች ሁሉ የሜምኖን ሃውልት ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም ይሉ ነበር::

ሜምኖን ዝናው እጅግ ከመግነኑ የተነሳ የተቀበረበት ስፍራ እኛ ዘንድ ይገኛል የሚለው ሽሚያ ከፍተኛ ነበር።

አንድ አፈታሪክ እንደሚለው፣ የአጽሙ ቅሪት መጀመሪያ ወደ ቆፕሮስ ደሴት ከተማ ወደነበረችው ፓፌስ ተወሰደ፣ ከዚያም ወደ ግሪኩ ደሴት ወደ ሮድስ ተሻገረ። እህቱ ሂመራ ወይም ሄመራ ሮድስ ድረስ መጥታ ወደ አሁኑ ሌባነን ወስዳ ፓሊዮኪስ በሚባል ስፍራ ቀበረችው። ሌሎች ደግሞ የተቀበረው ሶርያ ውስጥ በባዳስ ወንዝ ዳርቻ ፓልቶን በሚባል ስፍራ ነው ይላሉ።

አንድ ሌላ አፈታሪክ ደግሞ በጦርነቱ የተሳተፉት ኢትዮጵያውያን አስከሬኑን ካቃጠሉ በኋላ ቅሪቱን ለፕሪያም ወንድም ለቲቶነስ ሱሳ ወስደው አስረከቡት፤ እሱም ኤሰፐስ በሚባል ወንዝ ዳርቻ በጉብታ ላይ ቀበረው፤ አካባቢውም በሜምኖን ስም ሰየመው ይላል።

እንደ ጥንት ግሪኮች አፈታሪክ ደግሞ ሜምኖን የተቀበረው ሄለስፖንት (Hellespont) ነው። ስፍራው አውሮጳንና እስያን፣ እንዲሁም ሜዲትራኒያን ባህር ከጥቁር ባህር የሚያገናኝ በመሆኑ እጅግ ከፍተኛ ስትራተጂክ ዋጋ ያለው ስለመሆኑ አንድና ሁለት የለውም።

ለሜምኖን ወደር የሌላቸው ፋቡላዎች ተደርድረውለታል። ለትልቁ እስክንድር እንኳ የሜምኖን ያህል አልተነገረለትም።

ሜምኖን ያረፈበትን ቀን ለማስታወስ የሰማይ አማልክት ሃዘን ተቀምጠው ይውላሉ። ሄለስፖንት በሚገኘው መቃብሩ ላይ ሜምኖዳይድስ (Memnodides) የሚባሉ በሜምኖን ስም የተሰየሙ ደቂቃን መናፍስት (phantoms) ሁሌ እንዳንዣበቡበት ነው። መናፍስቱን መለኮታዊ ሃይል ያጎናጸፋቸው የጥንት ግሪኮች አማልክት ንጉስ ወይም የበላይ እራሱ ዜውስ ነበር። እነዚህ በአእዋፍ የተመሰሉ መናፍስት ውሃ ከኤሰፐስ ወንዝ በክንፋቸው እየጨለፉ በመቃብሩ ላይ ያንጠፈጥፋሉ።

መናፍስቱ የተፈጠሩት የሜምኖን አስከሬን በእንጨት ክምር ላይ ተደርጎ ሲጋይ ከተፈጠረው ትናኝና ከአሳቱ ፍም ነው። ሜምኖዳይዶቹ እንደተፈጠሩ የአስከሬኑን ማቃጠያ ስፍራ ሶስት ጊዜ ከዞሩት በኋላ በአራተኛው ዙር ለሁለት ተከፈሉና የእርስበርስ ጦርነት ገጥመው ተዋደቁ። አስከሬኖቻቸውም በማቃጠያው ላይ ተረበረቡና ለሜምኖን ክብር መስዋእት ሆኑ። ፋቡላው እንደሚለው በራሪዎቹ መናፍስት እስካሁንም ድረስ በየጊዜው ከመዋደቅና መስዋእት ከመሆን አልተቆጠቡም።

አፈታሪኩ ሜምኖን ቅላቱ እንደ ጢንዚዛ ጥቁር፣ (ebony black) ውበቱ ደግሞ ተወዳዳሪ የሌለው ነበር ይላል።

ጋኔን መልኩ ጥቁር ነው የሚለው ከዬት መጣ? የእነሜምኖን ክንድ ያዳሸቃቸው ወይም የደቆሳቸው ህዝቦች የዘሩት ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ይሆን? ገናናው የአሲሪያ ንጉስ ናቡከደነጾር እስራኤላውያንን ለባርነት ሲነዳ የሜምኖን የልጅ ልጆች ከፍተኛ ሚና ተጫውተው ይሆን? አይሁዶች ያኔ ይሆን ዲያቢሎስን ፈጥረው መልኩን ጥላሸት የቀቡትና ለዘረኞች ርዕዮተዓለማዊ መሰረት የጣሉላቸው? ብሎም ለባላንጣቸው ለሂትለር መነሳት መንገድ ያመቻቹለት? ታሪክ ሃቀኛ ነው፣ ይዋል ይደር እንጂ የእጅን አያሳጣም።

ታሪክ የገጠመኞች ጥርቅም ነው። አስቀድሞ በመለኮት የተተለመ አቅጣጫ አለው ከሚሉት ጎራ አይደለሁም። ለሁሉም ክስተት መንስኤ አለው። ዛሬ የምናከናውነው ወይም ሳናከናውነው የቀረነው የነገን ምንነት ይወስናል ከሚሉት ካምፕ ነኝ። ሜምኖን በድንገት ባይሞት ኖሮ ዓለምን ያንቀጠቀጠው ገናናው የሮማ መንግስት ይነሳ ነበር? ትሮይ ጦርነቱን ብታሸንፍ ኖሮ የግሪክ ስልጣኔ ያብብ ነበር? ምዕራባውያን አሁን የተጎናጸፉት የበላይነት እውን ይሆን ነበር?

ከ3300 አመት በፊት ኢትዮጵያውያኖች ሱሳ አካባቢ እንዴት ሊገኙ ቻሉ? በዚያን ዘመን መካከለኛው ምስራቅ የጥቁር ህዝቦችም መናኸሪያ ነበረ ማለት ነው? ከጊዜ በኋላ ተገፍተው ወጥተው ነው? ወይስ ቅላታቸው ተቀይሮ የነበሩበትን አካባቢ አሁንም እንደያዙት ናቸው?

ወዳጄ ዶክተር ሃይሉ ማሞ አሁን በሥራ ላይ ያለው እሳይ በተጠቀሰችው ጥንታዊቷ ሱሳ አጠገብ በካስፒያን ባህር አካባቢ ጆርጂያ ውስጥ ነው። ሰዎቹ የመጣነው ከኢትዮጵያ ነው ብለውታል። የቆዳቸው ቀለም ግን ነጭ ነው ወይም ሆኗል። በኢትዮጵያ ብቻ የሚሠራባቸው ጨ ቀ ጸ እነሱም እንደሚጠቀሙባቸው አጫውቶኛል። ሰዎቹ ታሪኩ የተደበቀው የታላቁ ሜምኖንና በሱ ዘመን የነበሩት ኢትዮጵያውያን ዝርያዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። የታሪክ ተመራማሪዎቻችን ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተውት ምርምር እንደሚያካሄዱ ተስፋ አደርጋለሁ።

የትሮይ ጦርነት ከተፈጸመ ከ700 አመታት በኋላ የፐርሺያው ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ዳርየስ (Darius I) ግሪክን ለመውረር ካዘመተው ከሃያ ሶስት አገሮች ከተውጣጣ ከ400000 ጦር ውስጥ በሁለት ምድብ የተከፈሉ ኢትዮጵያውያንም ነበሩበት። ከምዕራብና ከምስራቅ የመጡ

ብሎ ታሪክ መዝግቧቸዋል:: ከምስራቅ የመጡት ጸጉራቸው ለስላሳ ሲሆን ከምዕራብ የመጡት ደግሞ ከርዳዳ ነበር ይላል:: ስለጦረኞቹ የራስ ጎፈርና ዱላም ተጠቅሷል:: ኦሮሞዎች የመጣነው ባህርን ተሻግረን ነው የሚሉት እውነትነት አለው ማለት ነው?

የሰውን ልጅ ታሪክ አቅጣጫ በማስያዝ ረገድ የጥንት ኢትዮጵያውያን ያደረጉትን ወይም ያላደረጉትን (acts of commission or omission) ሌላ ታላቅ ምሳሌ ልጥቀስ:: በአክሱም ዘመነ መንግስት ቀይባህርን ተሻግሮ የአረቦችን መሬት ይገዛ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ሜካ ሲደርስ ያካባቢው ጎሳ መሪ የነበሩት የነቢዩ መሃመድ አያትን ያገኛል:: የጦሩ መሪ ከጎምቱው ጋር የወዳጅነት የሚመስል ውይይት ካካሄዱ በኋላ ምን እንዳደርግልዎ ይሻሉ? ብሎ ይጠይቃቸዋል:: «ጦርህ ግመሎቼን ወስዶብኛል፣ አስመልስልኝ» ይሉታል:: ሰውዬው ይገረምና «ሌላ ጥያቄ የለዎትም?» ብሎ ይጠይቃቸዋል:: አለመኖሩን ሲያውቅ «እኔስ ስለ ካባው (Kaba) ጥበቃ ጉዳይ ያነሳሉ ብዬ ጠብቄ ነበር» ቢላቸው፣ «ስለሱ እኔንና አንተን አይመለከተንም፣ ካባውን የራሱ አምላክ ይጠብቀዋል» አሉትና ተለያዩ:: (ካባው አብርሃም ልጁን ይስሃቅን ሊሰዋበት የነበረው ስፍራ ነው ተብሎ በጥንት አረቦችና ከዚያም በኋላ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ይታመናል:: እስላሞች ወደ ሜካ የሚጓዙት ካባውን ከዞሩ በኋላ ዲያቢሎስን ለመውገር ነው::)

ወራሪው የኢትዮጵያ ጦር የመሃመድን አባት ገድሏቸው ቢሆንና ካባውን ደግሞ የጣዖት ማምለኪያ ነው ብሎ አፈራርሶት ቢሆን ኖሮ የእስልምና ሃይማኖት የሚባል ነገር ላይኖር ይችል ነበር ማለት ነው:: በተመሳሳይ፣ ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን የተወለዱ የአይሁድ ህጻናት እንዲፈጁ በሄሮድ የታዘዘው ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ቢሆን ኖሮ የክርስትና ሃይማኖት አይኖርም ነበር:: የዓለም ታሪክም አሁን ከምናውቀው የተለየ ይሆን እንደነበር መገመት ከባድ አይደለም::

የተሻለ ወይስ የባሰ ዓለም? ለሚለው ጥያቄ መልሱን በእርግጠኛነት መናገር ባይቻልም አሁን ከምናውቀው ብዙም የተለየ አይሆንም ነበር እላለሁ:: ሰው በመሰረቱ ወዶ፣ ተወዶ፣ ኑሮውን አሸንፎ፣ በግራና በቀኝ ካለው ጋር ተስማምቶ በሰላምና በደስታ መኖር የሚፈልግ ፍጡር ነው:: ባንጻሩ፣ የሥልጣን ጥመኞችና ጨቋኞች እንዲሁም አልጠግብ ባዮች በየጊዜው እየተነሱ ህዝብን ማመሳቸው እንደማይቀር ሳይታለም የተፈታ ነው:: በታሪክ እንዳየነው ሥልጣንን አንስቶ የጫነ ልቡ ይደነድናል፣ ይባልጋል:: እራሱን ከህግ በላይ አድርጎ ከህዝብ አናት አልወርድ ይላል:: ይህ የነበረ፣ ያለ፣ ወደፊትም የሚኖር ነው:: ስለሆነም፣ በዚህም ምክንያት ተባለ በዚያ፣ መራኮት፣

መውደቅ፣ መነሳት ብሎም ትግልና ዋይታ፣ አልፎ አልፎም እፎይታ፣ የሰው ልጅ የማይላቀቃቸው ምድራዊ ዕጣዎቹ ናቸው።

ስለሆነም፣ ሰው በተአምር ወደ መልአክነት ካልተቀየረ በቀር በታሪክ አርኪቴክቸር ላይ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት አይቻልም። ለዚህ ነው የሮማ መንግስት፣ ክርስትና ወይም እስልምና ባይነሱ ኖሮ የዓለም ታሪክ አሁን ከደረሰንበት እጅግ የተለየ ይሆን ነበር ለማለት የማይቻለው።

ቢሆንም፣ ሊባል የሚችል ነገር ግን ይኖራል። ሁለቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች ባይነሱ ኖሮ የአመተ ምህረትም ሆነ የእስልምና ዘመን አቆጣጠር አይኖሩም ነበር። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንና በካቶሊክ ቤተክርስትያን መካከል ስለዘመን አቆጣጠር ክርክር አይነሳም ነበር። የ2000 ዓም መባቻን ለማክበር በዛሬው ዕለት እዚህ ብሮንሰን ሴንተር አንሰበሰብም ነበር። የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር መነሻው የክርስቶስ ልደት ሳይሆን ሌላ ይሆን ነበር። ምናልባት ንግስተ ሳባ የነገሰችበት አመት ይሆን ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ 3000ን ለማክበር በጉጉት እንጠብቅ ነበር። ስለሜምኖን የቀድሞ አባቶቻችን ያውቁ ከነበር ደግሞ ጀግናው የተወለደበት ቀን የዘመናችን መጀመሪያ ሊሆን ይችል ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ ዘንድሮ በኛ አቆጣጠር 3220 አመተ ሜምኖን ይሆን ነበር።

ክርስትናና እስልምና ባይነሱ ኖሮ የመስቀል ጦርነት አይኖርም ነበር። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በእምነታቸው ምክንያት አይገደሉም ነበር፣ ከቤታቸውና መንደራቸው ተፈናቅለው አይሰደዱም ነበር። የግራኝ መሃመድ ወረራ በኢትዮጵያ አይካሄድም ነበር። ኢትዮጵያ ከውጪው ዓለም ጋር የነበራት ሰፊ ግንኙነት ዳብሮ ስልጣኔዋ ከፍ ካለ ደረጃ ላይ ይደርስ ነበር። ቢን ላድን የኒው ዮርክን ህንጻዎች ደርምሶ ሽብርና ሽብርተኛነት የፖለቲካና ዜና መድረኮች አያጣብቡም ነበር።

የታሪክን ሂደት በተመለከተ ምን ጊዜም ቢሆን መዘንጋት የሌለበት የተሻለ ዕውቀት፣ የተሻለ መላ፣ የተሻለ መሳሪያ፣ የተሻለ መሪ የታደለ ህዝብ ለባላንጣው ተገዥ ላለመሆን ያለው ዕድል የሰፋ ነው። ትግል ስለማያከትም የሚሻለው ክንድንና ወኔን አፈርጥሞ መገኘት ብቻ ነው። አበሻ በርበሬውን ከተነጠቀ ግን የወኔው ነገር ካሁን በኋላ እንጃለት!

## ግሪጎሪያን ካላንደር

አሁን ወደ ጁሊየስ ሲዘረ ቀን አቆጣጠር እንመለስ። በየአራቱ አመት አንድ ቀን ይጨመር የተባለው ድንጋጌ በትክክል በሥራ ላይ ሳይውል ቀረ። ጭማሪው በየሶስት አመት ሆነና ውዥንብር ተፈጠረ።

ቤተክርስትያናት እአአ በ325 በኒቂያው ጉባኤ አንድ ወጥ ካላንደር ቢያጸድቁም በትክክል በተግባር ሳይተረጎም ቀረ።

የተሻሻለ ነው የተባለ ሌላ ካላንደር የሮማው ቤተክርስትያን እአአ በ530 አወጣ። ለማሻሻያው መሰረት የነበረው ዳዮኒስየስ የተባሉ መነኩሴ ያደረጉት የዘመን ስሌት ነበር። የቀን መቁጠሪያው የካቶሊክ ቤተክርስትያን በሚያዝባቸው ወይም በሚቆጣጠራቸው አካባቢዎች በጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ የመነኩሴው ስሌት ክርስቶስ የተወለደበትን ዘመን ቢያንስ በሰባት አመት እንዳስረዘመው ተደረሰበት። ይህ ስለመሆኑ ወይም ስህተት ስለመፈጸሙ በሊቃውንትና በቤተክርስትያን ሰዎች መካከል መተማመን ነበረ። ለስህተቱ እንደጉልህ ማስረጃ የተጠቀሰው፡-

<u>አንደኛ</u>፣ ቤተክርስትያን ክርስቶስ በተወለደበት አመት አዲስ ከዋክብት ታዩ እያለች ተሻሻለ እንደተባለው የቀን መቁጠሪያ ከሆነ ግን ኮከቦቹ የታዩበትን ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በ7 አመት ያስቀድመዋል። በነገራችን ላይ የከዋክብት ተማራማሪዎች እንደደረሱበት ታዩ የተባሉት ልዩ ኮከቦች ጁፒተርና ሳተርን ናቸው። ያለወትሮ ተጠጋግተውና ቦግ ብለው መታየታቸው ከክርስቶስ መወለድ ጋር ተገጣጠመ።

<u>ሁለተኛ</u>፣ ክርስቶስ በተወለደበት አመት የአይሁድ ህጻናት እንዲፈጁ ትእዛዝ ያስተላለፈው ንጉስ ሄሮድ ሆኖ ሳለ ተሻሻለ የተባለው የዘመን መቁጠሪያ ግን የንጉሱን ሞት ከክርስቶስ ልደት በአራት አመት ያስቀድመዋል።

የፋሲካን በአል አከባበር በተመለከተ፣ በአሉ የሚከበርበት ቀን እንደዘመን አቆጣጠሩ እየተዘበራረቀ ተቸግረው ስለነበር ጉዳዩ ያሳሰባቸው የካቶሊክ ቤተክርስትያን አባቶች ለረዥም ጊዜ የመፍትሄ ሃሳቦችን ሲያንከባልሉ፣ ሲያነሱና ሲጥሉ ከቆዩ በኋላ እአአ በ1582 ዓም የሮማው ጳጳስ ጎርጎርዮስ አስራሶስተኛው (Gregory XIII) ለሁሉም ክርስትያኖች የሚያገለግልና በጊዜው የነበሩትን ውዥንብሮች የሚያስወግድ አዲስ የዘመን አቆጣጠር ስርአትና የበአላት ቀኖች የሚቀመሩበት ዘዴ አውጥቻለሁና አይታችሁ አጽድቁልኝ ብሎ በመላው ዓለም ለሚገኙ የቤተክርስትያኑ ተጠሪዎቸ የስብሰባ ጥሪ አስተላለፈ። ከጎርጎርዮስ ሃሳቦች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ።

<u>አንደኛ</u>፣ በ1582 ከነበረው የኦክቶበር ወር አስር ቀኖች እንደሌሉ እንዲቆጠር ሆኖ ቀኖች እንዲሸጋሸጉ፣

<u>ሁለተኛ፣</u> የፋሲካ በአል የሚከበርበት ቀን ሳይዘበራረቅ ሁሉም ባንድ ቀን ማክበር እንዲችል የወጣውን አዲስ የቀን የመቀመሪያ ዘዴ ሁሉም እንዲከተለው፣

<u>ሶስተኛ፣</u> ከ1600 አመት በፊት ጁሊየስ ሲዘር የደነገገው በየአራቱ አመት የአንድ ቀን ጭማሪ ተግባራዊ እንዲሆን፣

<u>አራተኛ፣</u> 1582ን ሁሉም መነሻ አድርጎት ወደፊት እንዲጓዝ፣

የሚሉትና ለጉባዔው የቀረቡት ሃሳቦች ተቀባይነት አግኝተው ጸደቁ::: ውጤቱም አሁን የአውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር ወይም ግሪጎሪያን ካላንደር የምንለው ነው::

## <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን አቋም</u>

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ሊቃውንት የጎርጎርዮስን ሃሳቦች ከመረመሩ በኋላ የደረሱበት መደምደሚያና አቋም የሚከተለውን ነበር::

<u>አንደኛ፣</u> ጉባኤው ለዘመን መነሻነት ያጸደቀው 1582፣ ክርስቶስ የተወለደበትንም ሆነ ዓለም የተፈጠረችበትን ዘመን በትክክል የሚያንጸባርቅ ስላልሆነ የተጠቀሰው ዘመን ቁጥር በሰባት አመት ተቀንሶ አዲሱ መነሻ 1575 እንዲሆን፣

<u>ሁለተኛ፣</u> የፋሲካ በአል መቼ መከበር እንዳለበት የቀረበው ሃሳብ የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን የደነገገችውን የበአል አከባበር ደንብ የሚያፋልስ በመሆኑ፣ የራሳችንን ውድቅ አድርገን ከባህር ማዶ የመጣውን [ለዚያውም ከተፈታታኞችን ከካቶሊክ ቤተክርስትያን የተላከውን] የምንቀበልበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም፣

የሚል ጽኑ አቋም ያዙ::

የወሮቹ ስያሜም ቢሆን እነመስከረምና መጋቢት እያሉላቸው በሮማውያን አማልክትና ነገስታት ስሞች የተሰየሙትን እነኦገስትንና ማርችን እንዲቀበሉ የኛ ሰዎች ሲጠየቁ፣ ኢትዮጵያውያን በመሆናችን ስለኢትዮጵያዊ ስነልቡና ሌላ ማንም ስለማይነግረን፣ ጥያቄውን እንደክብረነክና ነጻነት መደፈር አይተውት ከሆነም ምንም አያስገርምም:: በኛው ዘመን ድንቅነሻችንን ፈረንጆች ሉሲ በሚል የፈረንጂ ስም ለዓለም ስላስተዋወቋት ምን ያህል እንደተብከነከንን ህያው ምስክሮች ነን::

በተጨማሪ፣ የግሪጎሪያን ካላንደር የወሮቹ ቀን ቁጥር የተለያየ በመሆኑ መጻፍና ማንበብ ባልተስፋፋበት አገር ካላንደሩ በሥራ ላይ እንዲውል ደንብ ቢወጣ ግራ መጋባት ሊከተልና ምስቅልቅል ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል:: ስለሆነም፣ የጾም ቀኖች በቀላሉ ሊገደፉ ይችላሉ:: ኩነኔም ሊከተል ነው:: ለዚህ ማነው ሃላፊነት የሚወስድ? በተጨማሪ፣ በስንት ልፋት የተጻፉና የተሰበሰቡ ስለበአል አከባበር የሚደነግጉ መጻህፍት ሊወገዱ አይደል? በኢትዮጵያ አቆጣጠር የተመለከቱ ዘመኖች፣ ወሮችና ቀኖች ባዲሱ ካላንደር መሰረት እንደገና ሊጻፉ ነው:: ይህን ለማድረግ ቢፈለግስ አቅሙ የታለ? ህዝቡስ፣ ለውጥ ለምን አስፈለገ? ብሎ ቢጠይቅ ፈረንጅ ስላዘዘ ነው ሊባል ነው? ነገሩ ሳይቸግር ጤፍ ብድር እንዳይሆን የያዝነውን እንደያዝን ብንጓዝ ይሻለናል ብቻ ሳይሆን የጎረጎርዮስን ካላንደር ላለመቀበል የወሰድነው አቋም ትክክል ነው ብላ ቤተክርስትያናችን ጸናች::

## ማጠቃለያ

አሁን ጉዳዩን እናጠቃለውና፣ የኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር የጥንት ግብጽና የጁሊየስ ሲዘር ስርአቶች ቅይጥ ነው:: አስራሁለቱ ወሮቻችንና አስራሶስተኛው ቁራጭ ወር፣ አመቱ የሚጀምርበት መስከረም አንድን ጨምሮ፣ ከጥንታዊቷ ግብጽ የተወሰደ ሲሆን ቁራጩ ወይም አስራሶስተኛው ወር በየአራቱ አመት አንድ ቀን እንዲጨመርለት የተደረገው ጁሊየስ ሲዘር የደነገገውን ስርአት ተከትሎ ነው:: የወሮችና ቀኖች ስያሜ ግን የኛው የኢትዮጵያውያን ነው::

ከሁለቱ ካላንደሮች የትኛው ነው ትክክል? የሚል ጥያቄ ሲነሳ መልሱ ቀላል ነው:: በዘመን መቁጠሪያ መሳሪያነታቸው ሁለቱም ካላንደሮች መነሻ ያደረጉት ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን አመት ነው:: ሁለቱም ካላንደሮች አንድ አይነት የአመት እርዝማኔ መለኪያ ተጠቅመው አውሮጳውያን ክርስቶስ ከተወለደ 2007 አመት ነው ሲሉ ኢትዮጵያውያን በበኩላችን 2000 ነው እንላለን:: ስለዚህ፣ ልዩነቱ ያለው ከመነሻው ላይ ነው ማለት ነው:: በ530 በአባ ዳዮኒስየስ አስሊነት የተደረገው የዘመን ማሻሻያ ወይም ማስተካከያ በሰባት አመት የተሳሳተ እንደነበር የማይታበል ሃቅ ሆኖ ሳለ በ1582 የተደረገው ጉባኤ ጉዳዩን፣ ተስማምተው እንትን ያደረጉት ነገር እንትን አይልም በሚል ፈሊጥ፣ አድበስብሶ አልፎታል:: የኢትዮጵያ ካላንደር ግን ተመሳሳይ ግድፈት የለበትም:: ስለዚህ፣ ትክክለኛው አቋም የኛ ቤተክርስትያን የወሰደችው ነው:: ለምድራዊ አስተዳደር ምቾት ሲባል ቤተክርስትያናችን እምነቷን ካቶሊኮች በዘረጉት ጠረጴዛ ላይ አጋድማ ለመሰዋት አልፈቀደችም::

**በዛሬው ቀን ብሎልን ካፍንጫችን ስር ርቆ የሚገኘውን የምድሩን፣ የሰማዩን፣ የሆነውን፣ ያልሆነውን በረዥሙ ስናማትር አምሽተናል:: በዚሁ መንፈስ፣ የሚቀጥለውን የሚለንየም በአል በአይነ ህሊናችን እንየው:: የልጅ ልጆቻችን ለእኩልነት፣ ለሰላም፣ ለፍቅር፣ ለፍትህ፣ ለእውነት ይገዙ ይሆን? ከመካከላቸው የዓለም ቤዛ ይወለድ ይሆን? ለዘለአለም የሚታወስ ሌላ ሜምኖን ይፈጠር ይሆን? ስለኛስ ምን ይሉ ይሆን? መስማማት ተስኗቸው አገር ያፈራረሱ እርጉሞች ወይስ የአገራቸውን አንድነት ለመጠበቅ የተዋደቁ ጀግኖችና ሃይማኖታቸው እንዳይገረሰስ የታገሉ አማኞች? ማን ያውቃል?**

**በትዕግስት ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ::**

**ኦታዋ፣ ካናዳ**
**<u>መስከረም 4፣ 2000 ዓም</u>**